# <u>የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ National Movement of Amhara</u>

11/10/2020

ወገንን የማዳን ጥሪ!

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ(አብን) በምስራቅ አማራ በሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ዞን ከ8 ወረዳዎች በላይ የተከሰተውን የአንበጣ መንጋ በተመለከተ የችግሩን አሳሳቢነትና ያደረሰውን ውድመት በመግለፅ መንግስት ሁሉንአቀፍ መፍትኄ እንዲሰጥ ማሳሰቡ ይታወሳል።

አሁንም ችግሩ ከመቀረፍ ይልቅ አድማሱን በማስፋት በአስቸኳይ እየተዛመተ በመሆኑ እና መንግስትም ለችግሩ መፍትኄ ከመፈለግ ይልቅ አንገብጋቢ ባልሆኑ ሌሎች ጉዳዮች በመጠመድ ለችግሩ ትኩረት ባለመስጠቱ ሕዝባችን ለከፍተኛ ችግር ተጋልጦ ይገኛል።

አብን የችግሩን አሳሳቢነትና ጊዜ አይሰጤነት በመገንዘብ ጉዳዩን የሚከታተል ኮሚቴ በማዋቀር በሁሉም አካባቢ የሚገኘው መዋቅር በተለያዩ መንገድ ወገን የማዳን ጥሪውን በብቃት እንዲወጣ ስምሪት ሰጥቶ ወደ ሥራ ገብቷል።
በቀጣይም ወገኖቻችን እስኪቋቋሙና ችግሩ በዘላቂነት እስኪፈታ ድረስ አብን የሚያደርገውን ሁሉንአቀፍ ድጋፍ አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን በተለያዩ አካባቢዎች የምትገኙ የአማራ ወጣት አደረጃጀቶችም ከንቅናቄያችን መዋቅር ጋር በመቀናጀት መላው ሕዝባችን በማስተባበርና ድጋፎችን በማሰባሰብ የበርሃ አንበጣውን በመከላከልና በበርሃ አንበጣው ሰብላቸው የወደመባቸውን ወገኖች በመደገፍ ኃላፊነታችሁን እንድትወጡ አብን ያሳስባል፡፡

መንግስትም ችግሩን መፍትኄ ለመስጠት እያሳየ ያለውን ቸልተኝነት በማስወገድ ችግሩን በአፋጣኝ ለመቅረፍ ሁሉንም አማራጮች በመጠቀም አስቸኳይ መፍትኄ እንዲሰጥና በአንበጣ መንጋው ሰብላቸው የወደመባቸውን ወገኖች መልሶ እንዲያቋቁም አብን በድጋሜ ጥሪውን ያቀርባል።

**አንድ አማራ ለሁሉም አማራ ፥ ሁሉም አማራ ለአንድ አማራ!**